በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር 2

የጽ/ቤቱ ዓላማ 4

የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር 4

የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሀይል አደረጃጀት 5

የፋይናንስ ምንጭ 5

የኦዲቱ ዓላማ 6

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች..................................... 6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.. .7

የኦዲት ወሰን.. 7

የኦዲት ዘዴ 8

የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description).................. 9

ክፍል ሁለት 13

ግኝቶች 13

ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ 13

ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ.. 15

በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ 16

ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ 17

የፈንድ ተጠቃሚዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ መስፈርት ስለመኖሩ 18

ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመለከተ..18

ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ 19

የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ..20

የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ መኖሩን በተመለከተ 21
ጥገናውን ለማስፈጸም እና ወጥ ለማድረግ የሚያስችል Guide Lines
and Procedure ተዘጋጅቶ ለመንገድ ኤጀንሲዎች መሰራጨቱን
በተመለከተ 26
የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች በወቅቱ ተቀጥረው
ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት
ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ..27
የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት
መኖሩን በተመለከተ ....
28
በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ
የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት መከናወኑን በተመለከተ 28
በጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ
መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ
መረጃ መኖሩን በተመለከተ...29
የመንገድ ደህንነት ስራ ስለመሰራቱና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት
ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ... 30
ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ.........................30
ክፍል ሦስት 33
መደምደሚያዎች 33
ክፍል አራት 36
የማሻሻያ ሀሳቦች 36
አባሪ 1 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት ....

የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. መንገድ ለአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ እና የመንገዶች ልማት ጥገናና ማሻሻያ ለሀገሪቱ የተቀላጠፈ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት አስፈላጊ ነው፡፡ መንገድ በአግባቡ ከተገነባ ለጉዞ ምቹ ስለሚሆን ጊዜን ከማሳጠሩም በላይ ለተሽከርካሪውና ለተጓዦችም ደህንነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይህ በመሆኑም መንገድ ከተሰራ በኋላ ለከፍተኛ ብልሽት ከመዳረጉ በፊት ጥገና ሊደረግለት ስለሚገባ ወጪውን ለመሸፈን ይረዳ ዘንድ የመንገድ ተጠቃሚዎችም ትኩረት በመስጠት የሚጠበቅብንን መወጣት ይኖርብናል፡፡ ለመንገድ ተጠቃሚው ጉዞው ምቹ እንዲሆን ለማስቻል የኢትዮጵያ መንገድ ፈንድ ከመንግስት እና ተጠቃሚውን በሚወክሉ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ተወካዮች በሚመራ የመንገድ ፈንድ ቦርድ እንዲተዳደር ተደርጎ በ1989 ዓ.ም. ተቋቁሟል፡፡

2. የመንገድ ጥገና በየጊዜው ካልተከናወነ እና ደህንነቱም ካልተጠበቀ በከፍተኛ ወጪ የተሰራው መንገድ በመበላሸት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከማስከተሉም በላይ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎችም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የመንገዶች ጥገና በቂና የማያቋርጥ የገንዘብ ፍሰት የሚሻ በመሆኑ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 66/1989 ዓ.ም. ተቋቁሟል፡፡

3. በአዋጁ መሠረት ፈንዱ የሚተዳደረው በቦርድ ሲሆን፣ ቦርዱም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት ቁጥርና የአወካከል ሥርዓት በመንግስት እንደሚወሰን ተገልጿል፡፡ በአዋጁ ላይ በተጠቀሰው መሰረት፣ ከክልሎች አምስት፣ ከመንገድ ተጠቃሚዎች የተወከሉ አራት አባላት እና በመንግሥት የተሰየመ አንድ ሰብሳቢ እና 7 አባላት በድምሩ በ2002 በጀት ዓመት የነበረው የቦርድ አባላት ብዛት

17 ነበር፡፡ ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 69/2003 መሰረት ለትራንስፖርት ሚኒስቴር መ/ቤት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

4. ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር 66/1989 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-
   - ✓ ፈንዱን ያስተዳድራል ፤
   - ✓ ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤
   - ✓ ለፈንዱ መግባት ያለባቸው ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውንና በፈንዱ ሂሳብ ውስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤
   - ✓ የመንገድ ኤጀንሲዎችን ዓመታዊ የመንገድ ጥገና ፕሮግራሞች ከመጽደቃቸው በፊት ይገመግማል፣ ፕሮግራሞቹም በተቀነባበረ እና በተቀናጀ ዘዴ እንዲዘጋጁ ያማክራል፣
   - ✓ በዓመቱ ውስጥ በፈንዱ የሚሸፈኑ ሥራዎችን ለመንግስት ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በዕቅዱ መሰረት የፈንዱን ገንዘብ ያከፋፍላል፤
   - ✓ በፈንዱ አከፋፈል ላይ ተጠያቂነትና ግልጽ አሰራር መኖሩን ያረጋግጣል፤
   - ✓ የመንገድ ኤጀንሲዎችን የሥራ አመራር ሪፖርቶች እየተቀበለ ይገመግማል፣ የፈንዱን አጠቃቀም በተመለከተ የሚጠናቀሩ ሪፖርቶችን አዘገጃጀት ይቆጣጠራል፤
   - ✓ በፈንዱ የተከናወኑትን የመንገድ ጥገና እና የመንገድ ደህንነት እርምጃዎች ተግባራት፣ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት ያስደርጋል፣ የኦዲት ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ በኦዲት ሪፖርቶቹ መሰረት ተገቢው እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤
   - ✓ ለመንገድ ጥገና ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የፋይናንስ ምንጮችን የታሪፍ ደረጃዎችን በተመለከተ ለመንግስት ሀሳብ ያቀርባል፤
   - ✓ ከመንገድ ጥገናና ከፈንዱ ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፤
   - ✓ በኦዲተር የተመረመረ የፈንዱ አመታዊ ሂሳብ እንዲጠናቀርና ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፤

- ✓ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤ ስራቸውን ይመራል፤ ያስተባብራል፡፡

የጽህፈት ቤቱ ዓላማ

5. ጽ/ቤቱ የተቋቋመበት ዓላማ ለመንገድ ጥገናና ለመንገድ ደህንነት እርምጃዎች የሚያስፈልጉትን ወጪዎች ለመሸፈን እና ለመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ መንገድ እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡

የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

6. ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት በአዋጁ ተሰጥቶታል፡፡
   - ✓ የቦርዱ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
   - ✓ የፈንዱን ሂሳብና ሪኮርዶች ይይዛል፣
   - ✓ የቦርዱን ሥራ አመራር ስብሰባዎች ሪኮርዶች ይይዛል፣
   - ✓ ለፈንዱ መግባት የሚገባው ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ በፈንዱ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣
   - ✓ የፈንዱን የሂሳብ መግለጫዎች እያዘጋጀ በየዓመቱ ለቦርዱ ያቀርባል፣
   - ✓ ስለፈንዱ ገቢዎችና አጠቃቀም፣ ስለመንገድ ጥገና ጠቀሜታ፣ መንገድን አለመጠገን ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች፣ ጥራት ያለው መንገድ ለተጠቃሚዎች ስለሚያስገኘው ቁጠባና ስለመሳሰሉት የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችንና ወቅታዊ ህትመቶችን ያመነጫል ፣ ያሰራጫል፣
   - ✓ የንብረት ባለቤት ይሆናል ፣ውል ይዋዋላል ፣በስሙ ይከሳል ፣ይከሰሳል፡፡

የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት

7. ቀደም ብሎ በመግቢያው እንደተገለጸው የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤትን በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ ሲኖረው የጽ/ቤቱ ሥራ ከቦርዱ በሚሰጥ አጠቃላይ መመሪያ መሰረት ይከናወናል፡፡

8. የጽ/ቤቱን ሥራ በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር አንድ ዋና ዳይሬክተር በስሩ ሁለት ፀሀፊዎች እና አንድ የህዝብ ግንኙነት ሰራተኛ፣ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ውስጥ

ኃላፊውን ጨምሮ አምስት የሰው ኃይል፣ ፋይናንስ እና ቴክኒካል ኦዲት ዳይሬክቶሬት ውስጥ ኃላፊው ጨምሮ ስምንት የሰው ኃይል፣ የፕላን ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ውስጥ ኃላፊውን ጨምሮ አራት የሰው ኃይል እና የጠቅላላ አገልግሎትን ተግባር የሚያከናውኑ ሁለት ሰራተኞች በድምሩ 23 የሰው ኃይል አሉት፡፡ ከጠቅላላ ሰራተኞች ውስጥ ሶስቱ በኮንትራት የተቀጠሩ (አንድ ሹፌር እና ሁለት የቴክኒካል ኦዲተሮች) ናቸው፡፡ በጽ/ቤቱ ካሉት ሰራተኞች ውስጥ 10 ሴቶች እና 13 ወንዶች ናቸው፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

9. ጽ/ቤቱ ተልዕኮውን ለማሳካት ከመንግስት መደበኛ በጀት፣ ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ፣ ከቅባት፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በተደረገ የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ክፍያና ጽ/ቤቱ የግምጃቤት ሠነድ በመግዛት ከሚገኝ ገቢ ለመንገድ ጥገና ሥራ እንዲውል ይደረጋል፡፡

10. ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከእነዚህ የፋይናንስ ምንጮች በመንገድ ጥገና ሥራ 2001 ዓ.ም ብር 1,588,704,600.00፣ በ2002 ዓ.ም ብር 1,604,995,000.00 እና በ2003 ዓ.ም ብር 1,283,102,000.00 እንደተመደበ ታውቋል፡፡ ነገር ግን ከተመደበው ገንዘብ ምን ያህል በሥራ ላይ እንደዋለ መረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሂሣቡ እንደማይጠቃለል እና ወጪው በጽ/ቤቱ እንደማይያዝ በመገለፁ የወጣውን ወጪ ማቅረብ አልተቻለም፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ የመንገድ ፈንድ አስተዳደር ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት የተመደበለትን በጀት በሥራ ላይ መዋሉን፣ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና በፈንዱ የሚገዙ ንብረቶች በአግባቡ መጠበቃቸውን፣ እንዲሁም ለህብረተሰቡ ስለመንገድ ጥገና ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መሰጠቱን እና ከመንገድ ኤጀንሲዎች ጋር ያለው የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት በመገምገም ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ሊያስከትሉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት በቀጣይ ፈንዱ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን

ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በማረጋገጥ የአሰራር ግድፈቶች ተስተካክለው ተግባራዊ ለመሆን የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

12. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (ጭብጦች) የተመረጡ ሲሆን፣ በሥራቸውም ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል እነርሱም፡-

1) ለመንገድ ጥገናና ደህንነት መሰብሰብ ያለበት ገንዘብ በአዋጁ መሠረት በትክክልና በወቅቱ መሰብሰቡን እና መመዝገቡን ማረጋገጥ፣
   - ❖ በጽ/ቤቱ ገቢዎች በሙሉ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢው ምዝገባም መከናወኑን ማጣራት፡-
   - ❖ የመንገድ ኤጀንሲዎች ለተላከላቸው ገንዘብ ተገቢውን መረጃና ምዝገባ ማከናወናቸውን ማጣራት፡-

2) በአገሪቱ ውስጥ የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ለመጠበቅ የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ፣ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉንና ከመንገድ ኤጀንሲዎች ጋር ጠንካራ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣
   - ❖ የመንገድ ጥገናና ደህንነት ለመጠበቅ የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ማጣራት፡-
   - ❖ የመንገድ ጥገናና ደህንነትን መንገዶች በብልሽት ከፍተኛ ጉዳት ሳይደርስባቸው በፊት ጥገናው መከናወኑን ማጣራት፡
   - ❖ በጽ/ቤቱ እና በመንገድ ኤጀንሲዎች መካከል የተዘረጋ የመረጃ ልውውጥ እና የአያያዝ ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን ማጣራት፡-
   - ❖ በጽ/ቤቱ እና በመንገድ ኤጀንሲዎች በኩል በፈንዱ የተገዙ ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውን እና ለታቀደው ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ፡-
   - ❖ የጽ/ቤቱ እና የመንገድ ኤጀንሲዎች የመረጃ ልውውጥ እና አያያዝ ስርዓት ጠንካራ መሆኑን በተመለከተ፡-

3) በጽ/ቤቱ በኩል ስለመንገድ ጥገና ጥቅም እና መንገድን አለመጠገን ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መሰጠቱን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

13. ለዝርዝር ኦዲቱ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 47 መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተው በጽ/ቤቱ አስተያየት ተሰጥቶበት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶችም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን

14. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ መንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በናሙና ተመርጠው ቀጥሎ በተዘረዘሩት የመንገድ ኤጀንሲዎች ነው፡፡

   1. በአማራ ክልል በሚገኙ ፍኖተሰላም፣ ባህርዳርና ጎንደር ማዘጋጃ ቤቶችና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን፣
   2. በኦሮሚያ ክልል የመንገዶች ባለስልጣን፣ ጅማ፣ ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና በኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የጅማ ጥገና ጽ/ቤት፣
   3. በደቡብ ብ/ብ/ ህዝቦች ክልል፣ የሀዋሳ ማዘጋጃ ቤት፣ በደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን የአርባምንጭ የጥገና ጽ/ቤት፣ ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት እና የደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን፣
   4. አዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እና
   5. ውክልና ተሰጥቷቸው ገቢ የሚሰበስቡ ኮሜት ትራንስፖርት፣ ወጋገን ባንክ፣ ኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት፣ ቶታል ኢትዮጵያና ሌሎች ድርጅቶች ነው፡፡

ኦዲቱ ዘዴ

15. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ለሚገኙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብና ዶክመንቶችን በመከለስ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ ከላይ በተጠቀሱት የመንገድ ኤጀንሲዎች እና የፈንዱን ገቢ ከሚሰበስቡ አካላት ጋር በአካል በመገኘት ቃለ መጠይቅ በማቅረብና ተያያዥነት ያላቸውን

ዶክመንቶች በመከለስ ነው፡፡ በተጨማሪም በናሙናው ላልተሸፈኑ ኤጀንሲዎች መጠይቆችን (Survey questionnaires) በመላክ መረጃዎችን ተሰብስበዋል፡፡

16. የሪፖርቱን ቅጂ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች ለመላክ ከጊዜ እና ከአሠራር ግንኙነት አንፃር የተመቸ ባለመሆኑ ጽ/ቤቱ ካለው የሥራ ግንኙነት አንፃር ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሁሉ የሪፖርቱን መልዕክት እንዲያስተላልፍ ይጠበቃል፡፡

የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description)

17. ሥዕል 1 በጽ/ቤቱ የፕላንና ጥናት የሥራ ሂደት ፍሰት ሥዕላዊ መግለጫ የሚያሳይ (Process description)

ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልገውን የፈንድ ጥያቄ/ፍላጎት መቀበል መረጃ ማደራጀት እና ጥናት ማካሄድ

ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልገውን የፈንድ ጥያቄ/ፍላጎት መቀበል መረጃ ማደራጀት እና ጥናት ማካሄድ

ክትትል ማካሄድ

የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

18. ሥዕል 2 በጽ/ቤቱ የፋይናንስ የሥራ ሂደት ፍሰት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ (Process description)

ገቢ መሰብሰብ

↓

የክፍያ ጥያቄዎችን በመቀበል ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ

↓

የሂሳብ ለመያ ቁጥር ሰጥቶ ምዝገባ በማከናወን ሰነዶቹን ፋይል ማድረግ

↓

ሂሳብ መዝጋት እና ሪፖርቶችን ማዘጋጀት

↓

ሒሳቡን በውስጥና በውጪ ኦዲተሮች ማስመርመር

19. <u>ሥዕል 3 በጽ/ቤቱ የቴክኒካል እና ፋይናንሻል ኦዲት የሥራ ሂደት ፍሰት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ (Process description)</u>



ክፍል ሁለት

ግኝቶች

1. ገቢዎች በሙሉ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢው ምዝገባም መከናወኑን በተመለከተ

ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ

20. ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 66/1989 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ አለበት፡፡

21. ይሁን እንጂ ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአዋጁ መሰረት በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በኩል እየተሰበሰበ በወሩ መጨረሻ ገቢ መሆን ሲገባው ገቢ አልተደረገም፡፡

22. ስለዚሁ ጉዳይ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው፣ በአዋጁ መሠረት ለመንገድ ጥገና የተጣለ የነዳጅ ታሪፍ የሚሰበሰበው እና በፈንዱ ሂሣብ ገቢ የሚደረገው በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በየወሩ መጨሻ ይሆናል ተብሎ የተደነገገ ሲሆን፣ ነባራዊ ሁኔታው ግን የነዳጅ ድርጅት በወሩ ውስጥ ከፈጸመው የነዳጅ ሽያጭ የሰበሰበውን የገንዘብ መጠን አጠቃሎ በቀጣይ ወር ላይ ገቢ እያደረገ የሚገኝ መሆኑ የገለጹ ሲሆን ይኸው ጥያቄ በደሰሳ ኦዲት ወቅት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ከነዳጅ ታሪፍ የሚሰበሰበው ገቢን በተመለከተ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በአዋጅ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በወሩ ውስጥ ከተሰበሰበ ገቢ በወሩ መጨረሻ ለጽ/ቤቱ ገቢ አይደረግም፡፡ አልፎ አልፎ ከአንድ እስከ ሁለት ወር ድረስ የሚዘገይበት አጋጣሚዎች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው በአዋጁ መሰረት ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በየወሩ መጨረሻ እየተሰበሰበ ገቢ የማይደረግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በሚያዝያ ወር/2011 ካከናወነው ሽያጭ ገቢ ያደረገው በሰኔ ወር/2011 ከመሆኑም ሌላ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ውስጥ ገቢ የተደረገበት መረጃ

ታይቶ በአማካኝ ከአንድ ወር እስከ ሁለት ወር የሚዘገይ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት በወሩ መጨረሻ ገቢ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

24. እንዲሁም ከቀድሞው ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተላለፈ መመሪያ መሰረት ከቅባት እና ዘይት መሰብሰብ ያለበት ገቢ በነዳጅ ማደያ ድርጅቶች በወቅቱ መሰብሰብና ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

25. ይህን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ተጠይቀው በነዳጅ ኩባንያዎች በኩል ከዘይትና ቅባት የሚሰበሰበው ገቢ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደዚህ የሥራ መስክ ከገቡት አዳዲስ ኩባንያዎች በስተቀር ነባሮቹ ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የሚያደርጉ ስለሆነ ከነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት የሚሰበሰበው ገቢ ከሞላ ጐደል ተስተካክሏል ለማለት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

26. ይህን አስመልክቶ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደዚህ የሥራ መስክ ከገቡት አዳዲስ ኩባንያዎች በስተቀር ነባሮቹ ወቅቱን ጠብቀው ገቢ እንደሚያደርጉ ቢገልጹም ለምሳሌ ቶታል ኢትዮጵያ በህዳር ወር/2010 ለፈጸመው ሽያጭ ብር 57,670.40 ገቢ ያደረገው በሰኔ ወር/2011 ሲሆን የሌሎች ወራት ገቢዎችም በወቅቱ በጽ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንደማይሆን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሌሎችም የነዳጅ ኩባንያዎች በወቅቱ እንደማያስገቡ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ በኦዲቱ ተገኝቶ ታይቷል፡፡

27. የኢትዮጵያ መንግሥት ከሱዳን እና ከጅቡቲ መንግስታት ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በውሉ መሰረት በወቅቱ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

28. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የመንገድ ጠቀሜታ ክፍያን ለመሰብሰብ ከኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር እና ከወጋገን ባንክ አክስዮን ማህበር ጋር የውል ስምምነት ያደረገ ቢሆንም ገቢው በውሉ መሰረት በወቅቱ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

29. እንዲሁም የኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር የሰበሰበው የውጭ ምንዛሪ በትክክለኛው የምንዛሪ ምጣኔ (rate) ገቢ ማድረጉን ለማረጋገጥ ኩፖኖቹ መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ መረጃ ባለመያያዙ ለማጣራት አልተቻለም፡፡ በውስጥ ኦዲት ክፍሉም በኩል ከኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር እና ከወጋገን ባንክ አክስዮን

ማህበር የሚገባው ገቢ በውል ስምምነቱ መሠረት በትክክለኛው የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ መግባቱን ለማረጋገጥ የተከናወነ የኦዲት ሥራ የለም፡፡

30. በተጨማሪም በሚያዝያ 18 ቀን 1998 ዓ.ም. በወጋገን ባንክ በኩል ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ገቢ ለመሰብሰብ የተወሰደው ባለ 10 ዶላር የኩፖን ቁጥር 0001 እስከ 0300 ብዛታቸው 300 የሚሆኑ ኩፖኖች እስካሁን ተሸጠው ገቢ ካለመደረጋቸውም በላይ ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች እና ከነዳጅ እና ቅባት የሚሰበሰበውን ገቢ ተገቢው ክትትል በማድረግ እና ከአንድ ሊትር የሚሰበሰበውን 10 ሣንቲም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል የሚችልበትን ሁኔታ ገቢን ከማሻሻል አንፃር ተጠንቶ ለውሳኔ ለመንግሥት አልቀረበም፡፡፡፡

31. ይህን በተመለከተ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከሁለቱም ድርጅቶች ጋር በተደረገው ውል መሠረት መሰብሰብ የሚገባው ገቢ አልተሰበሰበም በሚለው ሀሣብ የማይስማሙና አልፎ አልፎ ለተወሰነ ጊዜ ዘግይቶ ገቢ የሚሰበሰብበት ወቅት ሊኖር እንደሚችል ይህንንም ችግር ለመቅረፍ እስከ ቦታው ድረስ ኦዲተሮችን በመላክ ድርጅቶቹ ገቢውን በወቅቱ ለምን ገቢ እንደማያደርጉ ጥናት እንደተደረገ ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሥራው የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊ ከመንገድ ጠቀሜታ ገቢ የሚደረገውን በተመለከተ ወቅቱን ጠብቆ ገቢ መሆን ሲገባው ለተወሰኑ ወራት የሚዘገይበት ሁኔታ መኖሩ ይስተዋላል ብለዋል፡፡

32. ይሁን እንጂ ኃላፊው አልፎ አልፎ ከመዘግየቱ በስተቀር ወቅቱን ጠብቆ ይሰበሰባል በማለት ቢገልጹም በኦዲቱ ወቅት ባደረግነው ማጣራት ኩፖኖቹ ተሸጠው ገቢ ለመደረጋቸው ማስረጃ ካለመቅረቡም በላይ ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ መሰብሰብ ያለበት ገቢ በተገባው የውል ስምምነት መሰረት በወቅቱ የማይሰበሰብ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ችግሩን ለመቅረፍ በኦዲተሮች በኩል ጥናት የተደረገበት መረጃም አልቀረበም፡፡

ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ

33. ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰብ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ማጣራት ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 66/89 መሰረት

ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ነገር ግን እስካሁን ምንም ዓይነት ገቢ አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡

34. ይህን ገቢ ከሚሰበስበው አካል አንዱ በሆነው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከሞጆ ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ሠራተኞች እንደተረዳነው ከክብደት በላይ የጫነ ተሽከርካሪ ሲመጣ የቅጣት ወረቀት በመጻፍ ለፍርድ ቤቶች እንደሚተላለፍና ፍርድ ቤት የቅጣቱን መጠን ሲወስን አሽከርካሪው ቅጣቱን እንዲከፍል የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ሁለት እኩል ከክብደት በላይ የጫኑ አሽከርካሪዎች የተለያየ የቅጣት መጠን እንደሚያስከፍል እና ተሽከርካሪው ክብደቱን ይዞ የተጓዘውን ርቀት ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡

35. ከዚህ በተጨማሪ ከክብደት የጫኑ ተሽከርካሪዎችን ለመለየት የሚያስችል ሚዛን በሁሉም የመግቢያ እና የመውጫ በሮች ባለመኖሩ ተሽከርካሪዎቹ በትርፍነት የጫኑትን ጭነት እንዲያራግፉ በማድረግ በመንገዶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የማድረግ ሥራ አልተሠራም፡፡

36. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከክብደት በላይ የሚጭኑ ተሽከርካሪዎችን ለፍርድ ቤት አቅርበው ጽ/ቤቱ የሚዛን ጣቢያዎች በሚገኙበት ክልል የሚጥለው ቅጣት ለክልሉ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ቢሮ ገቢ ስለሚሆን ገቢው ወደ መንገድ ፈንድ የሚዞርበት ሁኔታ አስቸጋሪ ሂደት በመፍጠሩ አዋጁ ላይ ማሻሻያ የማድረግ ሂደት የተጀመረ በመሆኑ ይህ ባለመጠናቀቁ ገቢው ወደ መንገድ ፈንድ እየገባ አይደለም ብለዋል፡፡

37. ኃላፊው ይህን ቢሉም ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት የሚውለውን ፈንድ አስተማማኝ ለማድረግ አዋጁ ላይ ማሻሻያ የማድረግ ሂደቱን ጽ/ቤቱ በአዋጅ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን አጠናቀው ተግባራዊ መደረግ ሲኖርበት ተከናውኖ አልተገኘም፡፡

<u>በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ</u>

38. ጽ/ቤቱ በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

39. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 66/89 መሰረት በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ያልሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

40. በዚህ ረገድ የተሠራው በአዋጁ መሠረት ክብደት ላይ ከተመሠረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል ደንብና መመሪያ መዘጋጀቱና ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ መላኩ ሲሆን ይህም ቢሆን እስከ አሁን ተወስኖ ባለመምጣቱ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

41. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ይህን አስመልክተው በሰጡት መልስ፣ በመንግሥት እንዲወሰን እስከአቀረቡበት ጊዜ ድረስ የበጀት ዕጥረት ያልነበረ በመሆኑ ሊዘገይ እንደቻለና በሌላ በኩል በአዋጁ ላይ ስለተደነገገ ብቻ የሚሰበሰብ ከሆነ አላስፈላጊ የገንዘብ ክምችት ተፈጥሮ በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ጫና እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

42. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሁኔታው ሲጣራ፣ የገንዘብ እጥረት በመኖሩ የተነሳ ሁሉም ከተሞች ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ እንዲያገኙ አለመካተታቸው እና የመንገድ ጥገናውም ደረጃውን ጠብቆ እንዲከናወን ለማድረግ አለመቻሉ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው ባስተላለፈዉ መመሪያ እና ከመንገድ ጠቀሜታ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በውክልና ከሚሰበስቡት ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ባለመሰብሰቡ የመንገድ ጥገና ወጪን አስተማማኝ በማድረግ ላይ አሉታዊ ተጽኖ ከማስከተሉም በላይ ለመንገድ ጥገና ከጽ/ቤቱ የሚመደበው በጀት አነስተኛ በመሆኑ መንገዶች በወቅቱ ሳይጠገኑ መቅረታቸውን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በወቅቱም የማይጠገኑ መንገዶች ብልሽታቸው እጨመረ ስለሚሄድ ለጥገናው የሚጠይቀው ወጪ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በተሽከርካሪዎች ላይ ጉዳት ይደርሳል፡፡

43. በአጠቃላይ ጽ/ቤቱ አዋጁ ላይ በተቀመጠው ጊዜ፣ የቀድሞው ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ እና የመንገድ ጠቀሜታ ክፍያን ለመሰብሰብ በተደረገው የውል ስምምነት መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በወቅቱ እየሰበሰበ አለመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

2. የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ለመጠበቅ የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

44. ጽ/ቤቱ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

45. ይሁን እንጂ ከፈንዱ የተወሰደ ገንዘብ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱ፣ በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት ሲጣራ፣ በወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ይህኑኑ ለመከታተል የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶች የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ እየሠሩ አለመሆኑን፣ በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ በተባሉበት ቦታ የማይገኙ እና ክትትልም የማያደርጉ መሆኑንና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ ያላቸው የሰው ኃይል ከሚሠራው ሥራ ጋር ተመጣጣኝ ስላልሆነ የቁጥጥሩ ሥራ የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

46. በተጨማሪም በፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ከዚህ ቀደም ባካሄደው ጥናት ሪፖርት ላይ ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እንዲያስችል አማካሪ ድርጅት ቢቀጠርም በአዲስ አበባና በኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በሚገባ ስለመወጣታቸው ለማረጋገጥ በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖሩና እንዲሁም የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የፈንዱን አጠቃቀም በተመለከተ በመንገድ ኤጀንሲዎች የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ በበቂ ደረጃ አለማከናወኑን፣ የውስጥ ኦዲቱም በመንገድ ኤጀንሲዎች በመገኘት የሂሣብ ምርመራ ሥራ አለመሠራቱና በመስክ ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አለማከናወኑን በሪፖርቱ ላይ ተገልጿል፡፡

47. በአጠቃላይ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ብር 39,977,928.20 ለአማካሪ ድርጅቶች ክፍያ ወጪ የተደረገ ቢሆንም፣ የተቀጠሩት አማካሪ ድርጅቶች የማማከር

ሥራቸውን በተገቢው መንገድ ለማከናወናቸው የቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር ሳይደረግ የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከፈል መሆኑን በናሙና ከታዩ ኤጀንሲዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ሙያው የሚጠይቀው የቴክኒክ ባለሙያዎች የሌለው በመሆኑ ተገቢው የፕሮጀክቶች ብቃት ምዘና በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑና የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በዕቅዱ ላይ ቢታይም የፋይናንሻልና ቴክኒካል ኦዲት ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

48. ስለዚሁ ጉዳይ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሥርዓቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንና ለዚህም ማሳያው በየዓመቱ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ማስደረግና በመንገድ ኤጀንሲዎች በሚከናወኑ ሥራዎች የክፍያ ሰርተፊኬት የሚቀርብ በመሆኑ ስርዓት ስለመኖሩ እንደሚያረጋግጥና ይህ ማለት ግን መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች አይኖሩም ማለት እንዳልሆነ አስታውቀዋል፡፡

49. ይሁን እንጂ በኛ አስተያየት በውጭ ኦዲተሮች የተከናወኑት ኦዲቶች በሙሉ የፋይናንሻል ኦዲት በመሆናቸውና የቴክኒካል ኦዲቱን በተመለከተ በአማካሪ ድርጅቶች በኩል ይከናወናል የሚል ምላሽ ቢሰጥም ለክፍያ የሚቀርቡ ሰርተፊኬቶችም የሚፈርሙት በክልል የማማከር ሥራቸውን በተገቢው መንገድ እየሰሩ ስለመሆኑ የማይረጋገጥ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመለከተ፡፡

50. ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረብ ይኖርበታል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋይናንሻል እና የፊዚካል ዕቅዳቸውን ሲያቀርቡ ከሚመደበው በጀት ጋር የሚጣጣም ለመሆኑ በባለሙያ አለመታየቱ ታውቋል፡፡

52. ይህን አስመለክቶ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የመንገድ ጥገናው የፊዚካል ስራ እያንዳንዱ ተግባር የነጠላ ዋጋ/unit rate/ ያለው ስለሆነ ስራው በክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተረጋግጦ በተሰራው የስራ መጠን ክፍያ መፈጸም እንጂ በጀቱን ከተግባር ጋር ለማጣጣም መሞከር አይደለም፣ ይህ ሲባል ግን የተጋነነ አለመጣጣምም ከተከሰተ ጉዳዩ ሊታይ የሚችልበት አማራጭ ዝግ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

53. ይሁን እንጂ በኛ አስተያየት የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋይናንሻል እና የፊዚካል ዕቅዳቸውን ሲያቀርቡ ከሚመደበው በጀት ጋር የሚጣጣም ለመሆኑ በባለሙያ በቅድሚያ በዕቅድ ደረጃ አለመታየቱ የአሰራር ክፍተቶችን ይፈጥራል፡፡

ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈዉ ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

54. ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በወቅቱ ሊጸድቀና በዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡

55. ይሁን እንጂ ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚፈቀደው በጀት በወቅቱ ባለመጽደቁ፣ የበጀት ዓመቱ ከመግባቱ አንድ ወር አስቀድሞ የጸደቀው አመታዊ ዕቅድ እና በጀት ለመንገድ ኤጀንሲዎች በወቅቱ እንዲደርስ ባለመደረጉ፣ በናሙና በተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲሁም ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በመገኘት ባደረግነው ማጣራት የመንገድ ኤጀንሲዎች በተፈቀደው ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት ሥራቸውን ለማከናወን ያለመቻላቸውና በመንገድ ኤጀንሲዎች አፈጻጸም ላይ አልፎ አልፎ አሉታዊ ተጽኖ ማሳደሩም ታይቷል፡፡

56. ይህን በተመለከተ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመንገድ ፈንድ በጀት እጅግ ዘገየ ከተባለ በጣም ውስን በሆኑ ጊዜያት ከሐምሌ እስከ መስከረም ወራት ውስጥ በቦርድ ጸድቆ ለመንገድ ኤጀንሲዎች መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ ወይም ከዚያ በፊት የሚገለጽላቸው ሲሆን፣ ቦርዱ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ቢዘገይ እንኳን ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚፈቀደው በጀት መጠን ስለሚታወቅ በጽ/ቤት ደረጃ በዚያው መነሻ ኤጀንሲዎች ተገቢውን የዕቅድ ዝግጅት እንዲያደርጉ እንደሚደረግ፣ በሌላም በኩል የበጀት ዓመቱ ከመግባቱ አስቀድሞ ባይጸድቅም ከሐምሌ እስከ መስከረም የክረምት ወራት በመሆናቸው የጥገና ሥራ ስለማይከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. በእኛ አስተያየት ግን በሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሰነዳቸው ላይ በተቀመጠው እና በሀገሪቱ ውስጥ ባለው የበጀት ዝግጅት የአሠራር ሥርዓት መሠረት በጀቱ ወቅቱን ጠብቆ በቦርዱ ጸድቆ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በወቅቱ መተላለፍ ይገባው ነበር፡፡

የመንገድ ፈንድ ስትራቴጂክ ዕቅድ

አፈጻጸምን በተመለከተ

58. የተበላሹ የአስፋልት፣ የጠጠር እና የገጠር መንገዶች ጥገና ሽፋን በስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ ሊደረስ የታቀደበት የሽፋን መቶኛ መጠን ማደግ ወይም ከፍ ማለት አለበት፡፡

59. በጽ/ቤቱ ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት የተዘጋጀው የስትራቴጂክ ዕቅድ ሲታይ በእቅዱ ዓመት መጨረሻ (በ2002 ዓ.ም.) የመንገዶችን ጥራት ደረጃ በማሻሻል የአስፋልት፣ የጠጠር እና የገጠር መንገዶች ሁኔታ እንደቅደም ተከተላቸው አሁን ከሚገኙበት 43%፣ 31% እና 30% ወደ 80%፣ 60% እና 50% ለማሳደግ በዕቅዱ የተያዘ ቢሆንም ይህ ዕቅድ የጽ/ቤቱ ድርሻ በግልጽ ካለማሳየቱም በላይ አፈጻጸሙን ለመገምገም አልተቻለም፡፡

60. ስለዚሁ ጉዳይ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ይህ ግብ ሲቀመጥ በመንገድ ዘርፍ የልማት ኘሮግራም መሠረት በሚከናወነው የመንገዶች መልሶ ግንባታ፣ የደረጃ ማሻሻያ እና የጥገና ሥራዎች መንገዶቹ የሚገኙበት ሁኔታ በዕቅዱ ላይ ወደ ተመለከተው አሀዝ ከፍ ለማድረግ የተጣለ የዘርፉ የልማት ግብ እንደሆነና እንደ መንገድ ፈንድ ለዚህ ግብ ስኬት የፈንዱ የፋይናንስ አቅርቦት የማሳደግ ሥራ በተገቢው መንገድ ተግባራዊ የተደረገ እና ለዚህ ግብ ስኬት ተከታታይ የፋይናንስ አቅርቦት ሲደረግ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

61. ይሁን እንጂ የተያዘው ዕቅድ ለመንገድ ዘርፍ በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የዕቅድ ሽፋን እንዳለ በመውሰድ የተዘጋጀ በመሆኑና የጽ/ቤቱ ድርሻ ተለይቶ ባለመቀመጡ ጽ/ቤቱ የድርሻውን መወጣቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

62. የመንገድ ጥገና አማካይ የኪ.ሜ ወጪን መቀነስ የሚያስችል ስልት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

63. በተጨማሪም በጽ/ቤቱ ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት የተዘጋጀው የስትራቴጂክ ዕቅድ ሲታይ፣ የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በአስፋልት ጠጠር እና የገጠር መንገድ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው 20 ሺህ 15 ሺህ እና 5 ሺህ የሚገመተውን የመደበኛ ጥገና ወጪ በ2002 መጨረሻ ወደ 5 ሺህ፣ 5 ሺህ እና 3 ሺህ ዝቅ እንዲል የመንገድ ጥገና ሥራን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሥራት የተያዘው ዕቅድ ተግባራዊ አልሆነም፡፡

64. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ በሰጡት መልስ ይህ ዕቅድ ሲታቀድ የተደረገው በመንገድ ዘርፍ በሚካሄድ የማሻሻያ ሥራዎች በተለይ ከሎጀስቲክ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚስተዋለው ብክነት በመቀነስ አማካይ የኪሎ ሜትር ወጪው ሊቀንስ ይገባል በሚል እሳቤ የተጣለ ግብ እንደሆነና ከዚህ አንፃር ስኬት ሊመዘገብ እንዳልቻለ፣ በዚህ ግብ አጣጣል ወቅት ጥቅል የሁኔታዎች ዳሰሳ የመውሰድ እና ሁኔታዎችን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ማየት ተገቢ እንደማይሆን ልምድ ተወስዶበት በቅርብ ጊዜ በተዘጋጀው የስትራቴጂክ ሠነድ ላይ መሰል ስህተት እንደማይስተዋል ገልጸዋል፡፡

65. በስትራተጂክ ዕቅዱ ሲታቀድ የተነሱ ሁኔታዎች ባለመዳሰሳቸው የአማካይ የኪሎ ሜትር የመንገድ ጥገና ወጪ መቀነስ አልተቻለም፡፡

የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ መኖሩን በተመለከተ፣

66. ለመንገድ የጥገና ሂደት ወጥ የሆነ የጥገና ደረጃ ሊኖረው፣ በወጣው ደረጃ መሠረት ሊፈፀም እንደሚገባና፣ ለጥገናውም አስፈላጊው ግብዓትና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ ሊወሰንና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

67. የመንገድ ጥገና ደረጃ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በኩል እንደተዘጋጀ ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም፣ በኦዲቱ በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት መሠረታዊ የመንገድ ጥገና ደረጃን ተከትለው የመንገድ ጥገና ሥራዎች ወጥ (standardize) በማድረግ እየተጠገኑ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡ በናሙና ከተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች (በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን፣ እና በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም በባህርዳር፣ በጐንደር፣ በሀዋሣ፣ በጅማ፣ በወሊሶ እና በወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት) የመንገድ ጥገና ሂደት መሰረታዊ የጥገና

ደረጃ ኖሮት እንደማይከናወን ለመረዳት የተቻለና በጽ/ቤቱም በዚህ ዙሪያ የተከናወነ ተግባር አለመኖሩ ታዉቋል፡፡

68. ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የመንገድ ጥገና ኘሮጀክቶች ጥገናው የሚከናወንበት ደረጃ ባለመኖሩና፣ ለጥገና የሚጠቀሙበት ግብዓት እና ኘሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ ተወስኖ ተግባራዊ ባለመደረጉ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቶችም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ሳያደርጉ ተሰራ ተብሎ የቀረበውን የክፍያ ሰርተፊኬት ያለገደብ የሚያረጋግጡ በመሆኑ በጊዜ እና በዋጋ ከዕቅድ በላይ የሆኑት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ያመለክታሉ፡፡

69. ለዚህም የጫኖ-ጨንቻ መንገድ ጥገና ሥራ በ1997 ዓ.ም. የተጀመረ ቢሆንም በተያዘለት የጊዜ ገደብ እና የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በመደበለት በጀት ከብር 10,390,999.24 ተጨማሪ ብር 6,787,628.52 (የኘሮጀክቱን 74%) ተጠቅሞም ሊጠናቀቅ አለመቻሉን እና የመንገዱ ርክክብ አለመፈጸሙን በኦዲቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት (ጥቅምት/2004 ዓ.ም) ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለመመልከት ተችሏል፡፡ በጉብኝቱ ወቅትም መንገዱ በጐርፍ ምክንያት ለብልሽት እየተዳረገ እንደሆነ የታየ በመሆኑ፣ የሚመለከተው አካል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ገንዘብ የወጣበትን መንገድ አገልግሎት መስጠት ከማቆሙ በፊት የመፍትሔ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

ፎቶ ግራፍ 1 የጫኖ-ጨንቻ መንገድ ጥገና ሥራ በ1997 ዓ.ም. ተጀምሮ ርክክብ ያልተፈጸመ የመንገዱን አንድ ጎን የሚያሳይ

ፎቶ ግራፍ 2 የጫኖ-ጨንቻ መንገድ ጥገና ሥራ መንገዱ ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ ምስል

70. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን በሰንዶዴ ድልድይ ግንባታ ላይ የኮንትራት ውል ከመፈጸሙ በፊት በቂ ዲዛይን እና የአፈር ናሙና ጥናት ባለመደረጉ ምክንያት ከተያዘው በጀት በላይ ወጪ ያስወጣ መሆኑን እና በመስክ ጉብኝት ወቅት እንዳየነው አሁን ላለው ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ የአፈር መሸርሸሩን ለመከላከል የሚያስችል ስራ በአግባቡ እንዳልተሰራ ተመልክተናል፡፡

ፎቶ ግራፍ 3 የሰንዶዴ ድልድይ ላይ የአፈር መሸርሸሩን ለመከላከል የተሰራውን ስራ የሚያሳይ

71. በተጨማሪም በፈንዱ የፋይናንስ ድጋፍ የሚጠገኑ መንገዶችን በተመለከተ ከተከለሱ መረጃዎች መነሻነትና ጉብኝት በተደረገባቸው በደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን አርባምንጭ ጥገና ጽ/ቤት (ጨኖ ጨንቻ)፣ በኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ጅማ የጥገና ጽ/ቤት (ጅማ ሰንተማ)፣ በአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የጐንደር ጥገና ጽ/ቤት (ግራኝ በር አርባያ)፣ ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት (ሉቃስ ሆስፒታል ጀርባ ሰፈር ውስጥ ለውስጥ) እና ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት (ከጤና ጣቢያ መንገድ ውስጥ ለውስጥ) ከታዩት ጥቂቶቹ ሲሆኑ ከተከለሱ መረጃዎች ደግሞ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ በትግራይ ክልል ውስጥ በክልሉና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአለም ገና ቡታጅራ መንገድ ላይ በተከናወኑ የመንገድ ጥገናዎች የጥገናው ሥራ በሚካሄድበት ወቅት የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃ ያልተሠራላቸው፣ መሠረታዊ የዲዛይን ችግር ያለባቸው፣ ለጥገና የሚጠቀሙት ጥሬ ዕቃ ደረጃውን ያልጠበቀ እና የላብላቶሪ

ቴስት በሚያስፈልጋቸው የመንገድ ጥገናዎች አልፎ አልፎ አለመሰራቱ የታየ ሲሆን፣ ይህ ክፍተት የተፈጠረው ፈንዱን በሚያስተዳድረው ጽ/ቤት የመንገድ የጥገና ሂደት መንገዱ የሚጠገንበት መሠረታዊ የጥገና ደረጃና ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ባለመደረጉ ነው፡፡ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በመስክ ጉብኝት ወቅት የተወሰዱ የፎቶግራፍ ምስሎችን መመልከት ይቻላል፡፡

ፎቶ 4 በኦሮሚያ መንገዶች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ በ2003 በጀት ዓመት ደረጃዉን ሳይጠብቅ የተጠገነ መንገድ(ከጅማ ሰንተማ)

72. የመንገድ ጥገና ሲከናወን ለምን ደረጃውን የጠበቀ እንዳልሆነ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የጥገና ደረጃ ወጥነት እንዲኖረው የመንገድ ግንባታ ጥገና እና ደረጃ የማውጣት ስልጣን በአዋጅ የተሰጠው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ስለሆነ በባለስልጣኑ የወጣ የመንገድ ዲዛይን፣ ደረጃ ... የሚያጠቃልል (Road design and specification manual) ያለ በመሆኑ እና መንገድ ፈንድም ከዚህ የተለየ ደረጃ

የማውጣት ስልጣን የሌለው በመሆኑ እንዲሁም በተቆጣጣሪ አካል የወጣው የሚያሰራ ስለሆነ ድግግሞሽ ካልሆነ ሌላ ማውጣት አስፈላጊ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

73. ይሁን እንጂ ከላይ የተመለከቱት ችግሮች የደረሱት የመንገድ ጥገናዎቹ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባወጣው የመንገድ ጥገና ደረጃ መሰረት ደረጃውን ጠብቀው መከናወናቸውን ጽ/ቤቱ የማረጋገጥ ሥራ የማይሠራ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥገናውን ለማስፈጸም እና ወጥ ለማድረግ የሚያስችል Guide Lines and Procedure ተዘጋጅቶ ለመንገድ ኤጀንሲዎች መሰራጨቱን በተመለከተ፣

74. የመንገድ ጥገና ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያና ማስፈፀሚያ ሥርዓት (GUIDE LINE & PROCEDURE መሠረት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

75. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች ለመረዳት እንደተቻለው የጥገና ደረጃን ወጥ ከማድረግ አንጻር በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መመሪያና ስለአፈጻጸሙ ሥርዓት (Guide Lines and Procedures) ያልደረሳቸው ቢሆንም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የተዘጋጀ ቢኖርም በጽ/ቤቱ የሚመደብላቸው በገንዘብ አቅም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ መመሪያውን ተግባራዊ እንዳላደረጉ ተረድተናል፡፡ ይኸውም በአማራ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን፣ ባህርዳር፣ ጎንደር እና ጅማ ማዘጋጃ ቤት፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን እና የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን በጽ/ቤቱ በኩል ባይደርሳቸውም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ያወጣው መመሪያ ያላቸው ቢሆንም በመመሪያው መሠረት ለመፈፀም በጽ/ቤቱ የሚመደብላቸው በጀት አናሳነት የተነሳ በመመሪያው መሰረት ጥራት ያለው መንገድ ጥገና ለማድረግ አለመቻሉን የገልጹ ሲሆን በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ሀዋሳ፣ ወሊሶ፣ እና ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት ከጽ/ቤቱ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ እና የመንገድ ጥገና ደረጃን ወጥ ለማድረግ የሚጠቀሙት መመሪያ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

76. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የጥገና ደረጃ ወጥነት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባወጣው የመንገድ ዲዛይን እና ደረጃ የተገለጸ በመሆኑ ይህንን መነሻ በማድረግ ኤጀንሲዎች ተገቢውን እንዲፈጽሙ ከማሳሰብ በተጨማሪ በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በኩል እነዚህ የተዘጋጁት ማኑዋሎች እና መመሪያዎች ለሁሉም እንዲደርስ እንዲሁም በስብሰባዎች ላይ ገለጻ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

77. ይሁን እንጂ በመስክ ጉብኝት ወቅት የታዩት የመንገድ ኤጀንሲዎች በሙሉ ከጽ/ቤቱ መመሪያና የአፈጻጸም ሥርዓት እንዳልደረሳቸው የገለፁ ሲሆን ጽ/ቤቱ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባዘጋጀው መመሪያ መሠረት መጠቀማቸውን አለማረጋገጡ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

78. የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

79. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች (ከፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በጽ/ቤቱ ባደረገው ጥናት ሪፖርት፣ ጫንጮ ላይ የመንገድ ፈንድ የፋይናንስ መመሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሪፖርትና ግንቦት 24 ቀን 2003 በተደረገው የመስክ ጉብኝት ሪፖርት) እንደታየው የኮንሰልታንት ቅጥር በወቅቱ እንደማይፈጸም፣ ከተቀጠሩ በኋላም ከአማካሪ ድርጅት ጋር የተፈረመውን ውል አፈጻጸም ለመከታተል የተዘረጋ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ እንዲሁም በኦዲቱ በተጎበኙ ክልሎች በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት በዞን እና በወረዳ ደረጃ መንገድ ባለስልጣን መዋቅር ያለው ቢሆንም በጅማ ዞን ያሉ የመንገድ ባለሥልጣኑ ሠራተኞች ከአማካሪዎች ጋር የተገባውን ወጪ እንዲያውቁት ባለመደረጉና ተባብረው የሚሰሩበት ስርዓት ባለመዘርጋቱ የበኩላቸውን ድጋፍ አለማድረጋቸውን በአነጋገርናቸው ወቅት ገልጸውልናል፡፡ ለዚህም አማካሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣታቸው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር እንደማይሠራ፣ በውላቸው መሰረት ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን የሰው ኃይል እና ሎጂስቲክ በማሟላት ስራውን እያከናወኑ አለመሆናቸው ታውቋል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አማካሪ ድርጅቶቹ በውላቸው ላይ በተቀመጠው መሰረት የመንገድ ጥገና መከናወኑ የመከታተል እና የመቆጣጠር ስራ በበቂ ሁኔታ ባለመሠራቱ፣ ለመንገድ ጥገና መጠቀም የሚገባቸውን ግብዓት የማይጠቀሙና ደረጃውን የጠበቀ የጥገና ስራና የውሃ ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ ባለመሠራታቸው በከፍተኛ ወጪ የተጠገኑ መንገዶች ማገልገል ከሚገባቸው ጊዜ በታች ግልጋሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

80. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጽ/ቤቱ ፋይናንስ የሚደረጉ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ጥገናው የሚከናወንበት ደረጃ፣ ለጥገና የሚጠቀሙበት ግብዓት እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ በአማካሪ ድርጅቶችም ሆነ በጽ/ቤቱ በኩል ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግ እና አማካሪ ድርጅቶችን የሚቆጣጠሯቸው መንግስታዊ ድርጅት የሆኑት የመንገድ ኤጀንሲዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

81. ይሁን እንጂ በኛ አስተያየት ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር የተፈረመውን ውል አፈጻጸም ለመከታተል የተዘረጋ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ሳይኖር፣ የአማካሪ ድርጅቶቹን ቅጥር ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉት መንግስታዊ ድርጅቶች (የመንገድ ኤጀንሲዎች) መሆናቸው ብቻ ዋስትና አለመሆኑ፣ ለመንገድ ጥገና አማካሪ ድርጅቶችን ለመቅጠር ለወጣው ወጪ ተመጣጣኝ ግልጋሎት አለመገኘቱና በጽ/ቤቱ በኩልም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ

82. የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በጽ/ቤቱ የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ካለመደረጉም በላይ ለመንገድ ጥገና ለተከፈለው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩን እና በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች ላይ የሚደረገው ወቅታዊ ክትትልም ጠንካራ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

83. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በጣም ውስን በሆነ የሰው ኃይል የሚንቀሳቀስ በመሆኑ የአማካሪ ቅጥር ክትትል እና ቁጥጥር በውክልና የመንግስት ተቋም ለሆኑ የመንገድ ኤጀንሲዎች የተሰጠ በመሆኑ እና ለአማካሪዎቹም ክፍያ የሚፈጸመው የመንገድ ኤጀንሲዎቹ አስተያየት ሲሰጡ እና በትክክል ስራ ላይ የነበሩ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ለአማካሪዎቹ ክፍያ የሚፈጸም በመሆኑ ቁጥጥር እንደሚደረግና በተጨማሪም ከ2001 አስከ 2003 በጀት ዓመት ላይ በተለያዩ ጊዜያት የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ለመንገድ ጥገና ቁጥጥር ሲወጡ የአማካሪ

ድርጅቶችን እንቅስቃሴም ላይ ቁጥጥር እንደሚደረግ የገለጹ ቢሆንም የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን ኃላፊ አማካሪ ድርጅቶቹ በተባሉበት ቦታ የማይገኙና ክትትልም በአግባቡ የማይደረግ መሆኑን፣ የወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አማካሪ ድርጅቶቹ የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ እየሠሩ አለመሆናቸውንና የአማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን አማካሪ ድርጅቶቹ ያላቸው የሰው ኃይል ውስን በመሆኑ የቁጥጥሩ ሥራ የሚፈለገውን ያህል እንደማይሠራ ገልጸዋል፡፡

84. ከዚህ በተጨማሪም በጫንጮ የመንገድ ፈንድ የፋይናንስ መመሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሪፖርት ላይ ከመንገድ ኤጀንሲዎች የመጡ ተሳታፊዎች በቡድን ባደረጉት ውይይት ላይ በአማካሪ ድረጅቶች ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ማጣራት በኦዲት ክፍሉ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የክትትል እና የቁጥጥር ስራ በዕቅድ ተይዞ አለመከናወኑንና በናሙና በተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች በተደረገ የመስክ ጉብኝት በተደረገው ማጣራት በአማካሪ ድርጅቶች ላይ በቂ ክትትልና ቁጥጥር እንዳልተከናወነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት መከናወኑን በተመለከተ

86. በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒካል ኦዲት በውስጥ የኦዲት ክፍሉ በዕቅድ በመያዝ መከናወን አለበት፡፡

87. ይሁን እንጂ በክፍሉ የኦዲት ወሰን ውስጥ(ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት) ጽ/ቤቱ ካከናወናቸው የክትትል እና የቁጥጥር ስራዎች ዋና የሆነውን በመንገድ ኤጀንሲዎች የተከናወኑ የፊዚካል እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንሻልም ሆነ የቴክኒካል ኦዲት አላከናወነም፡፡

88. ስለ ጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ በሰጡት መልስ፣ በዕቅድ ተይዞ በየዓመቱ በሁሉም ኤጀንሲዎች ላይ የፋይናንሻል ኦዲት እየተደረገ መሆኑንና ቴክኒካል ኦዲትም በከፊል የተደረገባቸው ኤጀንሲዎች ያሉ፣ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ለማካሄድ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው፣

የፋይናንሻል እና የቴክኒካል ኦዲት በዕቅድ ተይዞ እንደማይከናወን በመግለጽ የማይከናወንበትን ምክንያትም በሥራዎች መደራረብና መብዛት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

89. ስለሆነም በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒካል ኦዲት በክፍሉ በዕቅድ በመያዝ አለመከናወኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ መኖሩን በተመለከተ

90. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ መቼና በምን ያህል ወጪ እንደተጠገኑ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ የመንገድ ጥገና መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ የጽ/ቤቱ ሁሉም በመንገድ ኤጀንሲዎች ስለሚያስተዳድሯቸው መንገዶች የሚገልጽ (የመንገዶችን አይነት፣ ርቀት፣ ደረጃ ፣የጥገና ታሪክ፣ በምን ያህል ወጪ እና መቼ እንደተጠገኑ...) የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ተይዞ አልተገኘም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የጥገና ታሪክ የሚገልጽ መረጃ በመስክ ጉብኝት በታዩት የመንገድ ኤጀንሲዎች ጭምር ተይዞ አልተገኘም፡፡

92. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ ላይ በጽ/ቤት ደረጃ በየሁለት አመቱ የመንገድ ኤጀንሲዎች የሚያስተዳድሯቸውን መንገዶችና መንገዶቹ የሚገኙበትን ሁኔታ (Road Condition Servey) እንዳለና መረጃ የሚያቀርቡ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

93. ስለሆነም የጥገና ታሪክ መረጃ መያዝ ተገቢውን ስራ እና ውሳኔ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን ወሳኝ በመሆኑ መረጃዉን አለመያዙ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመንገድ ደህንነት ስራ ስለመሰራቱና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

94. ጽ/ቤቱ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት ፈንዱ ለመንገድ ደህንነት ፕሮግራም መዋል አለበት፡፡ መንገድ ኤጀንሲዎች በፈንዱ የመንገድ ደህንነት ስራ ማከናወን እንዲችሉ

ለማድረግ እንዲሁም በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ደህንነት ዙሪያ እንዳልሠሩና በሚመለከታቸው አካላትም ቢሆን መሠራት ያለበትን ያህል አለመሠራቱን የመስክ ጉብኝት ባደረግንባቸው መንገዶች (ጨኖ ጨንቻና ከወላይታ በዳውሮ ጅማ) መንገዶቹ ጠመዝማዛና አስቸጋሪ ሆነው ሣለ ምንም ዓይነት የመንገድ ላይ ምልክት ካለመታየቱም በላይ በሌሎቹም አውራ መንገዶች ላይ በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የተሠራው ሥራ አጥጋቢ አይደለም፡፡ በጽ/ቤቱም በኩል ለመንገድ ኤጀንሲዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አለመደረጉና በጀትም እንዳልተያዘ ባደረግንላቸው ቃለ መጠይቅ (ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት፣ ጅማ ማዘጋጃ ቤት፣ የደቡብ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የአማራ ክልል ገጠር መንገዶች ባለሥልጣንና የባህርዳር ከተማ ማዘጋጃ ቤት) ለማወቅ ችለናል፡፡ በመሆኑም ከመንገድ ደህንነት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለመምጣቱ እንደ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

96. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተደጋጋሚ የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን የሠራና ከኤጀንሲዎች ጋር ባለው የጋራ መድረክ የሚገመገም ተግባር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገ ውይይት ላይ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በየካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የተዘጋጀው ቀርቦልናል፡፡

97. ይሁን እንጂ የካቲት 28 ቀን 2002 የተዘጋጀው የምክክር ጉባኤ የመንገድ ኤጀንሲዎችን አፈጻጸም እንጂ በመንገድ ደህንነት ላይ እንዳልነበረ ከቀረበልን ጋዜጣ ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የያዙት ዕቅድ እንደሌለና የመንገድ ደህንነት ሥራ ማከናወን እንዳለባቸውም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በጽ/ቤቱ ስላልተከናወነና ተደጋጋሚ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች መሠራቱን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ

98. በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት ለማጠናከር፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና የተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ ሊዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው ሁሉ ሊደርስ ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳውቅ መረጃ አዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት በሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት፣ በመንገድ ኤጀንሲዎችና በአማካሪ ድርጅቶች በኩል ግልጽ የሆነ እና የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ በመንገድ ኤጀንሲዎች እና በጽ/ቤቱ መካከል የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር እና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ፈንድ ከመስጠቱ በፊት ውል ሊዋዋል እና ለኤጀንሲዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎችም በውሉ መሰረት እንዲፈጸሙ አልተደረገም፡፡

100. ይህን በተመለከተ የጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሰጡት መልስ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት የሚገልጽ መረጃ አዘጋጅቶ በተደጋጋሚ ጊዜ እንደተሰራጨና ከዚህም በተጨማሪ በመንገድ ፈንድ አዋጅ ላይ ጽ/ቤቱ ምን ምን እንደሚሠራ የተገለጸ ከመሆኑም በላይ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየዓመቱ በሚደረገው የምክክር ጉባኤ፣ ለባለሙያዎች በሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይ እንዲሁም በየጊዜው ለባለድርሻ አካላት በሚተላለፉ መመሪያዎች ላይ ይህ ተግባር በትክክል እንደሚሰራ አስታውቀዋል፡፡

101. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና መርጠን የመስክ ጉብኝት ባደረግንባቸው (በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ አዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን አማራ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን፣ ባህርዳር፣ ፍኖተ ሰላም፣ ወሊሶ፣ ጐንደር፣ ጅማ፣ ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት) የመንገድ ኤጀንሲዎች ሁሉ አልፎ አልፎ በሚጠሩ አንዳንድ ስብሰባዎች ላይ ከሚነገራቸው ውጪ መረጃው ተዘጋጅቶ እንዳልደረሳቸው የገለጹ ሲሆን ለኛም ለመሰራጨቱ መረጃው አልቀረበልንም፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያዎች

102. ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ:

- ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሠረት ከነዳጅ ታሪፍ መሰብሰብ ያለበት ገቢ በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት አማካኝነት ወደ ፈንዱ ሂሳብ በየወሩ መጨረሻ ገቢ አለመሆኑ፣
- ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሠረት ከክብደት በላይ ከሚጭኑ ተሽከርካሪዎች ከሚሰበሰበውቅጣት ገቢ መሰብሰብ ሲገባው አለማሰባሰቡ፣
- ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሠረት ከክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ በጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- ኢትዮጵያ ከሱዳን እና ከጅቡቲ መንግስታት ጋር የገባችውን የሁለትዮሽ ውል መሰረት በማድረግ ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ በመሰብሰብ ለመንገድ ጥገና የሚውል ሲሆን ይህንን ገቢ እንዲሰበስቡ ኮሜት ትራንስፖርት እና ወጋገን ባንክ አክስዮን ማህበሩ ከጽ/ቤቱ ጋር ውል የገቡ ቢሆንም ገቢው በውሉ መሰረት ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ እና ገቢው ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያድግ ጽ/ቤቱ አለመስራቱ፣

103. የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ለመጠበቅ የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

- ጽ/ቤቱ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣

- ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና በባለሙያ አለመረጋገጡ
- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚፈቀደው በጀት በወቅቱ አለመጽደቁ፣ የጸደቀው አመታዊ ዕቅድ እና በጀት ለመንገድ ኤጀንሲዎች በወቅቱ እንዲደርስ አለመደረጉ፣
- የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ በ2002 ዓ.ም. መጨረሻ የመንገዶችን ጥራት ደረጃ በማሻሻል የአስፋልት፣ የጠጠር እና የገጠር መንገዶች ሁኔታ እንደቅደም ተከተላቸው አሁን ከሚገኙበት 43%፣ 31% እና 30% አማካይ 32% ወደ 80%፣ 60% እና 50% ለማሳደግ በስትራቴጂክ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በተያዘው ዕቅድ መሠረት ካለመፈጸሙም በላይ የጽ/ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ አለመታየቱ እና በመንገድ ፈንድ ያልተዘጋጀን እቅድ የሴክተሩ ዕቅድ ሆኖ መቅረቡ፣
- የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በአስፓልት ጠጠር እና የገጠር መንገድ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው 20 ሺህ 15 ሺህ እና 5 ሺህ የሚገመተውን የመደበኛ ጥገና ወጪ በ2002 መጨረሻ ወደ 5 ሺህ፣ 5 ሺህ እና 3 ሺህ ዝቅ እንዲል የመንገድ ጥገና ሥራን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሥራት የተያዘው ዕቅድ ተግባራዊ አለመሆኑ እና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የታዩ ጉዳዮች አለመታየታቸው፣
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የወጣውን መሠረታዊ የጥገና ደረጃ የመንገድ ኤጀንሲዎች አለመጠቀማቸው፣ ለጥገና መጠቀም የሚገባቸው ጥሬ ዕቃ እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ ግልጽ በሆነ መልኩ ተቀምጦ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የመንገድ ጥገና ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል GUIDE LINE & PROCEDURE መሠረት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች በወቅቱ ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎችን አለመከናወኑ፣

- በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት በዕቅድ ተይዞ አለመከናወኑ፣
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምን ያህል ወጪ መቼ እንደተጠገነ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ አለመያዙ፣
- ጽ/ቤቱ የመንገድ ኤጀንሲዎች በፈንዱ የመንገድ ደህንነት ስራ ማከናወን ይችሉ ዘንድ እና በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣
- በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያውን የሥራ ግንኙነት፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና የተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አለመድረሱ፣

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

104. ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፣

- ጽ/ቤቱ በአዋጁ እና በውሉ መሰረት ገቢዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ በዕቅድ ሊሰራ፣ በአዋጁና እና በውሉ መሰረት ገቢዎችን በሙሉ በወቅቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡
- ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል::
- በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

105. የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ለመጠበቅ የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣

- ጽ/ቤቱ ለመንገድ ለጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፡፡
- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡
- በጽ/ቤቱ የሚዘጋጀው የስትራቴጂክ ዕቅድ ከመንገድ ዘርፍ አጠቃላይ የልማት ኘሮግራም በመነሳት በጽ/ቤት ደረጃ ሊሠራ የሚቻለውን በመለየትና በተያዘው ዕቅድ መሠረት በመፈጸም የጽ/ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ሊካተት ይገባል፡፡

- የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በስትራቴጂክ ዕቅድ ከመዘጋጀቱ በፊት በቂ የሆነ ጥናት ላይ የመሠረተና ሊተገበር የሚችል ሊሆን ይገባል፡፡
- የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ፣ ለጥገና መጠቀም የሚገባቸው ጥሬ ዕቃ እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ ግልጽ በሆነ መልኩ በማስቀመጥ ወጥ የሆነ የጥገና ደረጃ ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የመንገድ ጥገና ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል GUIDE LINE & PROCEDURE ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች በወቅቱ ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ጽ/ቤቱ የሚከናወኑ የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎችን በየዓመቱ በማቀድ የፋይናንሻል እና የቴክኒክ ኦዲት ማከናወን አለበት፡፡
- በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት በዕቅድ በመያዝ መከናወን አለበት፡፡
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምንያህል ወጪ መቼ እንደተጠገነ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ የመንገድ ኤጀንሲዎች በፈንዱ የመንገድ ደህንነት ስራ ማከናወን ይችሉ ዘንድ እና በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና የተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

- ጽ/ቤቱ በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስራዎችን በማከናወን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ ለመንገድ ኤጀንሲዎች እና መረጃ በመስጠት ላደረጉልን የሥራ ትብብር ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ 1

<u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርት</u>

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- <u>የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት</u>

የኦዲት አካባቢ፡- <u>የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ</u>

የኦዲት ጭብጦች /Audit Issues/	የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/
1. በጽ/ቤቱ ገቢዎች በሙሉ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢው ምዝገባም መከናወኑን በተመለከተ	1. ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰብ አለበት፡፡
	2. ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	3. በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
2. መንገድ ጥገናና ደህንነትን ለመጠበቅ የተገኘዉ ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን በተመለከተ	4. ከመንገድ ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ዝርዝር አመታዊ የሥራ ዕቅድ ሊቀርብ ይገባል፡፡
	5. ጽ/ቤቱ ፈንድ ተጠቃሚዎችን ለመመርጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ የመመርጫ መስፈርት ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
	6. የተዘጋጀውም መስፈርት በተወሰነ ጊዜ ሊከለስ ይገባል፡፡
	7. የሥራ ዝርዝር ዕቅድ ሳይቀርብ ፈንድ መለቀቅ የለበትም፡፡
	8. ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ ዕቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡
	9. ለበጀትና የሥራ ፕሮግራም ዝግጅት ግልጽ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	10. ከጽ/ቤቱ ለመንገድ ለኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ሂሳብ ተለይቶ ሊመዘገብ ይገባል፡፡
	11. የመንገድ ኤጀንሲዎች ከመንገድ ፈንድ የሚላክላቸውን ገንዘብ ለይተው ሊመዘግቡ

	ይገባል፡፡
	12. የመንገድ ኤጀንሲዎች በሚያስተዳድሩት መንገድ መጠን መሰረት ፍትሃዊ የፈንድ ስርጭት እንዲኖር ለማድረግ የስርጭት መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	13. ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ጥገናው የሚከናወንበት ደረጃ፣ ለጥገና የሚጠቀሙበት ጥሬ ዕቃ እና ፕሮጀክቱ የሚወስደዉ ጊዜ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡
	14. ከፈንዱ የተወሰደ ገንዘብ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	15. ከሚመደበዉ በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ ዕቅድ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፡፡
	16. የፕሮጀክት ብቃት ምዘና ለሁሉም ፕሮጀክቶች መደረግ አለበት፡፡
	17. የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች ሊቀጠሩ ይገባል፡፡
	18. ጽ/ቤቱ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ፈንድ ከመስጠቱ በፊት ውል ሊዋዋል ይገባል፡፡
	19. በጽ/ቤቱ በኩል ለኤጀንሲዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎች በውሉ መሰረት መፈጸም አለባቸዉ፡፡
	20. የፈንዱን ገንዘብ ከተመደበዉ የወጪ አርዕስት ዉጭ ሥራ ላይ መዋል የለበትም፡፡
	21. የፈንዱን ሂሳብ ከመንገድ ጥገናና ደህንነት ዉጪ አዛዉሮ መጠቀም የለበትም፡፡
	22. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያላቸዉን የስራ ድርሻ የሚገልጽ መረጃ ሊዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡
	23. የተበላሹ የአስፋልት መንገዶች ጥገና ሽፋን በስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ ሊደርስ የታቀደበት የሽፋን መጠን ፐርሰንቴጅ ማደግ አለበት፡፡
	24. የተበላሹ የጠጠር መንገዶች ጥገና ሽፋን በስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ ሊደርስ የታቀደበት የሽፋን መጠን ፐርሰንቴጅ ማደግ አለበት፡፡

	25. ከጠጠር መንገድ ውጭ የሆኑ የተበላሹ የገጠር መንገዶች ጥገና ሽፋን በስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመቱ መጨረሻ ሊደርስ የታቀደበት የሽፋን መጠን ፐርሰንቴጅ ማደግ አለበት፡፡
	26. የመንገድ ጥገና አማካይ የኪ.ሜ ወጪን መቀነስ የሚያስችል ስልት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	27. የመንገድ ጥገና ሂደት መሰረታዊ የጥገና ደረጃ ሊኖር እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	28. የጥገና ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል GUIDE LINE & PROCEDURE ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	29. ጽ/ቤቱ ከኤጀንሲዎች ወቅታዊ ሪፖርት ሊያገኝ የሚችልበትን ስርዓት መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
	30. በመንገድ ኤጀንሲዎች የሚጠናቀረዉ የየሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለጽ/ቤቱ መድረስ አለበት፡፡
	31. የመንገድ ኤጀንሲዎች ከመንገድ ፈንድ የወሰዱትን ገንዘብ አስመልክቶ በውጭም ሆነ በውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ አስተያየቶች ላይ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት እና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡
	32. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን በሚመለከት የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡
	33. በመንገድ ኤጀንሲዎች ፕሮጀክቶች ለመንገድ ጥገና የሚውሉ ተበላሽተው የቆሙ በፈንዱ የተገዙ መሣሪያዎች በአግባቡ ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡
	34. በፈንዱ የተገዙ እና በመንገድ ኤጀንሲዎች የሚጠበቁ ንብረቶች በሌላ በጀት ከተገዙ ንብረቶች ጋር ተለይተዉ ሊመዘገቡ ይገባል፡፡
	35. በፈንዱ የተገዙ ንብረቶች ካለ አገልግሎት ከሚቀመጡ አማራጭ አገልግሎት የሚሰጡበት መንገድ መመቻቸት አለበት፡፡
	36. የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖር አለበት፡፡
	37. በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና ግምገማ ሥርዐት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

	38. በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት መከናወን አለበት፡፡
	39. ከመንገድ ኤጀንሲዎች የተሟላ የሂሳብ መግለጫ በየወሩ መላክ አለበት፡፡
	40. ጽ/ቤቱ የሚያከናወናቸው የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎች ታቅደው ሊከናወኑ ይገባል፡፡
	41. በመንገድ ፈንድ መንገዶች ተጠግነው ከአገልግሎት ዘመናቸው በፊት ለሚደርስባቸው ጉዳት የጥገና ሽፋን ከማግኘታቸው በፊት ምክንያቱ ተጣርቶ፣ ተጠያቂው መለየት ይኖርበታል፡፡
	42. የመንገድ ላይ ምልክትቶች ሲሰሩ ደረጃቸዉን ጠብቀው ሊሰሩ እና በአግባቡ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
	43. በመንገድ ኤጀንሲዎች እና በመንገድ ጥገና ኮንትራክተሮች (ሥራ ተቋራጮች) እንዲሁም በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መካከል ግልፅ የሆነ የሥራ ግንኙነት ፤ ኃላፊነት እና የተጠያቂነት ሥርዓት መኖር አለበት፡፡
	44. አንድ መንገድ ከመጠገኑ በፊት ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች የጥራት ክትትል ማረጋገጫ በቅድሚያ በአማካሪ ድርጅቶች /በባለሙያ/ መሰጠት አለበት፡፡
2. በጽ/ቤቱ በኩል ስለመንገድ ጥገና ጥቅም እና መንገድን አለመጠገን ስለሚያስከትላቸዉ ጉዳቶች ለህብረተሰቡ የገንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መሰጠቱን ማረጋገጥ	45. ጽ/ቤቱ ስለ ፈንዱ ገቢዎች እና አጠቃቀም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት አለበት፡፡
	46. ስለ መንገድ ጥገና ጥራት ያለው መንገድ ለተጠቃሚው ስለሚያስገኘው ቁጠባ እና ተያያዥ የሆኑ ጠቀሜታዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ (ወቅታዊ ህትመቶችን ማመንጨት እና ማሰራጨት የመሳሰሉ) ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
	47. በመንገዶች ላይ ተሽከርካሪዎች ከክብደት በላይ በመጫን ምክንያት የሚያስከትሉትን የመንገድ ጉዳት በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መሰራት አለበት፡፡